# ደደቢት ብድር እና ቁጠባ ተቋም አ/ማ

## የ 2023/24 የስራ አፈፃፀም ሪፖርት በቦርድ ሊቀመንበር

## በባለ አክሲዮኖች 18ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ የሚቀርብ

ጥር 2025

**መቐለ**

## 1. ጥቅል ሪፖርት (Summery Report)

ደደቢት ብድር እና ቁጠባ ተቋም ከለው 200 ቅርንጫፎች እና ንኡስ ቅርንጫፎች ውስጥ በዚህ በጀት ዓመት 2023/24 ስራ የጀመሩት 154 (76.5%) ሲሆን የቀሩት 45(22.5%) ግን ከወራሪዎች ነፃ ስላልወጡ ስራ ሊጀምሩ አልቻሉም ። ዋና ቢሮ፣ ዞኖች እና ቅርንጫፎች ጨምሮ ከ ጠቅላላ 209 ቅርንጫፎች እና ንኡስ ቅርንጫፎች 112 (53.5%) ኮር ባንኪንግ ሲስተም ገብቶለት በኔትዎርክ የሚሰሩ ናቸው ። የተቀሩትን ከጠላት ስር ካሉት ውጭ በሂደት ይገኛሉ ።

እንደ ተቋም ያለን ቋሚ ሰራተኛ ብዛት 3,358 ከዚህ 42.8% ሴቶች ሲሆኑ ኮንትራት ቅጥር ደግሞ 110 ሁኖ ከዚህ 18% ሴቶች ናቸው ። የተቋማችን ግዝያዊ እና ቋሚ ሰራተኛ ድምር 3,468 ሲሆን ከዚህ 42% ሴቶች ናቸው።

የኦፐረሽን መደቦች አፈፃፀም በሚመለከት ቁጠባ በዚህ ዓመት 297,851 አዳዲስ ቆጣቢ ደንበኞች ያፈራን ሲሆን በጠቅላላ ደግሞ 1.656 ሚልዮን የሚሆኑ የቆጣቢዎዝ ብዛት አለ። በገንዘብ ሲታይ ደግሞ በሰኔ በነበረው 13.089 ቢልዮን ብር ድምር ቁጠባ (Ballance) በ 0.826 ቢልዮን ብር በመጨመር አሁን ያለው ቀሪ ቁጠባ 13.915 ቢሊዮን ብር ሁኗል። ይህ በፐርሰንት ሲገለፅ በዚህ አመት ጠቅላላ ቁጠባ 30% ለመጨመር እቅድ ተይዞ በ 6.31% ከነበረው ጨምሯል።

ብድር መስጠት በሚመለከት በዚህ ዓመት ለ27,493 ደንበኞች 3.985 ቢልዮን ብር የተሰጠ ሲሆን እቅድ ከ ፍፃሜ ጋር ሲነፃፀር በሰው በ 19% በገንዝብ ደግሞ በ 57% ብቻ ነው ተፈፅሞ ያለው። ብድር ማስመለስ ሲታይ ደግሞ 3 ቢልዩን ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ የነበረ ሲሆን በዚህ ዓመት እንደ ተቋም በተደረገው 175 ሚሊዮን ብር የወለድ ምህረትና ሌሎች ማትግያዎች በመጨመር ፍፃሜ 2.977 ቢልዮን ብር ሊመለስ ችሏል። ይህ በፐርሰንት ሲገለፅ 99% ከእቅዳችን አኳያ ሊመለስ ችሏል።

ያለው የብድር ውዝፍ መጠን ሲታይ በሰኔ 2015 ዓ/ም የነበረ የውዝፍ መጠን 6.322 ቢልዮን ብር ሲሆን በዚህ ዓመት ወደ 5.075 ቢልዮን ብር ሊወርድ ችሏል። የተወሰኑ የብድር ዓይነቶች የውዝፋቸው መጠን በመቀነስ ላይ ያሉ እንኳ ቢሆኑም ሌሎች የብድር አይነቶች ደግሞ የውዝፍ መጠናዝው በመጨመር ላይ ይገኛሉ ። በተቓም ደረጃ በቢሄራዊ ባንክ በተሰጠ ማስተካከያ መሰረት በሰኔ መጨረሻ 2015 ዓ/ም የነበረ ጠቅላላ የሃብት መጠን 18.752 ቢልዮን ብር ሲሆን ቀሪ ብድር 9.954 ቢልዮን ነው። በበጀት ዓመት 2016 መጨረሻ ያለው የተቋሙ ጠቅላላ 11.968 ቢልዮን ብር ሲሆን ቀሪ ብድር 10.950 ቢሊዮን ብር ሁኗል። ይህ በንፅፅር ሲገለፅ የተቋሙ ጠቅላላ ሃብት ካለፈው በጀት ዓመት 2015ዓ/ም በ 6.784 ቢልዮን ብር ሲቀንስ ቀሪ ብድር ደግሞ በብር 0.996 ቢልዮን ጭማሪ አሳይቷል ። በአጠቃላይ ተቋማችን በዚህ ዓመት **1.297** ቢልዮን ብር ትርፍ ያሳየበት ምክንያት የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ባደረገው የብድር ማሻሽያ ምክንያት እንዲሻሻል በመደረጉ እንጂ ተቋማችን አሁን ባለበት እንቅስቃሴ በኪሳራ እንዳለ ነው የሚያሳየው።

## 1. መግቢያ

ደደቢት ብድር እና ቁጠባ ተቋም አ/ማ በክልላችን ከሚንቀሳቀሱ የፋይናንስ ተቋማት አንድና የመጀመርያ የማይክሮ ፋይናንስ ተቋም ሲሆን በለፉት 30 ዓመታት ሰፋፊ የፋይናንስ ችግሮች በመቅረፍ የስራ ዕድሎች በመፍጠር ድህነትን በመቀነስ ጉልህ ስፍራ ሲጨወት የነበረ እና ያለ የፋይናንስ ተቋም ነው። ተቋማችን በገጠር እና በከተማ ፣ በጥቃቅን የእርሻ ስራዎች ፣ በጥቃቅን እና አነስተኛ፣ እንዲሁም መካከለኛ የንግድ ተቋማት መሰረት ያደረገ የፋይናንስ አቅርቦት እየሰጠ ያለ የፋይናንስ ተቋም ነው። ይሁን እንጂ ተቋማችን ለሕ/ሰቡ የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት ዘመናዊ ኮር ባንኪንግ ቴክኖሎጂ በማስገባት እንዲሁም ወደ ባንክ ለማሳደግ የዝግጅት ስራዎች በምትሰራበት ወቅት ባለፈው 2/3 ዓመታት ጦርነት በማጋጠሙ ከባድ የሰው እና የሃብት ኪሳራ ደርሶባታል ።

ይህ እንዳለ ሁኖ ከፕሪቶሪያው ስምምነት በኋላ የተሻለ ሰላም ስለተገኘ አብዛኛው ቅርንጫፎቻችን ወደ ስራ የገቡ በመሆናቸው በጦርነቱ ምክንያት የደረሰ ጉዳት በውጭ አማካሪዎች እንዲጠና ተደርጎ ከደረሰው ጉዳት ለማገገም ሪከቨሪ እቅድ (Recovery plan) ተዘጋጅቶ እንዲፀድቅ በማድረግ ከ ነሐሴ 2015 ዓ/ም ጀምሮ ወደተግባር ተገብቶ እየተሰራበት ይገኛል ። በዚህ መሰረት ከሐምሌ 01/2023 እስከ ሰኔ 30/2024 ባለው ግዜ እንድ ተቋም እና በየ ክፍሉ የተፈፀሙ መደቦች እንደሚከተለው ተዘጋጅቶ ቀርቧል።

- የዚህ ሪፖርት ባለቤት ፡- ደደቢት ብድር እና ቁጠባ ተቋም አ/ማ
- የዚህ ሪፖርት አጭር ማብራርያ ፡- ይህ ሪፖርት የዋና ቢሮ ደደቢት ብድር እና ቁጠባ ተቋም አ/ማ የ2015/16 ዓ/ም በጀት ዓመት የእቅድ አፈፃፀም የሚያሳይ ሪፖርት ነው።
- የሪፖርቱ አላማ **፡-** መደባት ኣፈፃፀማ የ2015/16 ዓ/ም በጀት ዓመት የስራ መደቦች ከእቅድ እና ፍፃሜ በማነፃፀር የቀረበ ሲሆን ከዚህ የተገኙ ጠንካራ አፈፃፀሞች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ እና ደካማ ኣፈፃፀም የታየባቸው ስራዎች ደግሞ እንዲሻኻሉ ለማሰቻል አላማ ያደረገ ነው ።

## 3. በቁልፍ መደብ የተያዙ ግቦች እና አፈፃፀማቸው

**3.1.** የአቅም ግንባታ መደብ አፈፃፀም፡- ይህ መደብ በተቋማችን ውስጥ እና ከተቋማችን ውጭ የተሰጡ ስልጠናዎች የሚያጠቃልል ሁኖ አመራር እና ባለሙያዎች ያላቸውን የአፈፃፀም አቅም እና ብቃት በማሳደግ በአገልግሎት አሰጣጥ ተቋማችን የተሻለ እንዲሆን ነው። በዚህ መሰረት በዚህ ዓመት የተሰጠ ስልጠና አንደ ተቋም ሲታይ፡-

- ✓ የስልጠና ፍላጎት የዳሰሳ ጥናት በማካሄድ በዚህ ዓመት 2656 ሰራተኞች የተለያየ የአቅም ግንባታ ስልጠና እንዲወስዱ የታቀደ ሲሆን ኣፈፃፀሙ ሲታይ ደግሞ 3553 ነው። ከዚህ ውስጥ 1387 ሴቶች ሁነው በኮር ባንኪንግ ፣ ድጅታል ሰርቪስን እና ሌሎች በውስጥ አቅም ስልጠና እንዲያገኙ የተደረገ ሲሆን በውጭ አካል ደግሞ በ ገንዘብ ፍሰት፣ ኮርፖሬት ጋቨርናንስ፣ ካስተመር ሰርቪስ፣ ሶሻል ኢንቫርኖሜንትና ወዴፐ፣ ክረዲት ኣናሊሲስን ፖርቶፎሊዮ ማናጂሜንትና ሌሎች እንዲሰለጥኑ በማድረግየነበረውን የኣቅም ውሱንነት እንዲሟላ ተደርጓል። ከዚህ በተጨማሪ ለ 224 ሰራሕተኞች ደግሞ ኦሬንቴሽን እንዲያገኙ ተደርጓል።
- ✓ የኔትዎርክ ፣ ድጋፍ ኣይቲና ኤሌክትሪሻን የተውጣጣ የሰው ሃይል ወደ ኣዲስ ኣበባ በመሄድ የተሟላ የልምድ ልውውጥ እንዲያገኝ ተደርጓል።

# 4. የአበይት መደቦች አፈፃፀም

## 4.1. የኦፕሬሽን መደቦች አፈፃፀም

### 4.1.1. የብድር መስጠት ስራዎች

- ✓ በበጀት ዓመት 2023/24ብድር በመስጠት ላይ ለ144,344 ደንበኞች 7 ቢሊዮን ብር **እንዲሰጥ እቅድ** ተይዞ ለ 27,493 ደንበኞች 3.985 ቢልዮን ብር እንዲሰጥ ተደርጓል። ይህ ካለፈው አመት ሲነፃፀር በ2014/15 ዓ/ም የተያዘ ግብ ሰላም ይሆናል የሚል ግምት ስለነበረ ነው ይሁን እንጂ ወደ ዳግም ጦርነት ስለተገባ እና ተቋሙ በእቅድ የያዘው ስራ ሊሰራ አልቻለም። የሰላም ውል ከተፈረመ በኋላ ግን ብድር የመስጠት ስራ በመስራት አፈፃፀሙ ወደ 0.313 ቢልዮን ብር እንዲሆን ችሏል። ስለዚህ በዚህ አመት የተሻለ ሰላም በመኖሩ ከተያዘው እቅድ 57% እንዲፈፀም ተችሏል። የዝቅተኛ የእቅድ አፈፃፀምምክንያት ብድር በበቂ ሁኔታ አለመመለሱ ፣ የመንግስት ድጋፍ መቀነሱ እና እንዲሁም በማህበረሰቡ ላይ ከባድ የኢኮኖሚ ጉዳት በመድረሱ እቅዱ ግቡን ሊመታ አልቻለም።
- ✓ በዚህ ዓመት ብድር ለመስጠት ምቹ ሁኔታ ባለመኖሩ በተወሰኑ የብድር ዓይነቶች እንደ መደበኛ ፣ እሙን ፣ ቢዝነስ ፣ ደመወዝተኛ ፣ ቤት መስርያ ፣ ወዴብ ፣ ኣውድና የሰራሕተኛን በተወሰነ እንቅስቃሴ እንዲሰራ ተችሏል ። ይህ ካለ መንግስት እና አጋዥ አካላት በተቋማችን ብቻ የተሰራ ነው ።

### 4.1.2. ብድር መመለስ በሚመለከት

**ሰደቓ1፡- የብድር መመለስ እና የቀሪ ውዝፍ ብድር በበጀት ዓመት2015/16 ካለፈው በጀት ዓመት 2014/15ዓ/ም ጋር ሲነፃፀር**

| ዓይነት | 2014/15 ዓ/ም ኣመላለስ በቢልዮን ብር | | 2015/16 ዓ/ም ኣመላለስ በቢልዮን ብር | |
|---|---|---|---|---|
| | ምሊሲት | ቀ/ው/ብድር | ምሊሲት | ቀ/ው/ብድር |
| እቅድ | 1.902 | 3.036 | 3 | 2.404 |
| ፍፃሜ | 0.4009 | 6.322 | 2.977 | 5.075 |
| % | 21 | 208 | 99 | 211 |
| ከ 2014/ ያለ ጭማሪ /ቀነስ | | | 2.576 | -1.247 |

- ✓ በዚህ ዓመት ብድር ለመመለስ የተያዘ እቅድ 3 ቢልዮን ብር ሲሆን ተቋማችን ባደረገው የወለድ ምህረት 175 ሚሊዮን ብር ፍፃሜ 2.977 ቢሊዩን ብር ወይም ደግሞ 99% ከተያዘው እቅድ እንዲፈፀም ተችሏል። ይህ ካለፈው በጀት ዓመት 2014/15 አፈፃፀም ጋር ሲነፃፀር የ 2.576 ቢሊዮን ብር ጭማሪ አሳይቷል።
- ✓ በዚህ ዓመት ከእቅድ አንፃር እጅግ ዝቅተኛ የብድር የአመላለስ ካላቸው የብድር አይነቶች ስናይ ተዘዋዋሪ (6%) ፣አውድ (45%) ፣ ገጠር ፓኬጅ (68%)፣ ዋስትና ፈንድ (69.5%) ሊሆኑ ችሏል።
- ✓ በቀሪ ውዝፍ ብድር ሲታይ ደግሞ በዚህ ዓመት የተያዘ እቅድ 2.404 ቢሊዮን ብርእ ሰሲሆን ፍፃሜ ደግሞ 5.075 ቢልየን ብር ቀሪ ውዝፍ ብድር ሊጨምር ችሏል። ይህ ካባለፈው በጀት አመት 2014/15

ሲነፃፀር በብር 1.247 ቀሪ ውዝፍ ብድር ሊቀንስ ችሏል። የዚህ ዓመት ዓመት አፈፃፀም ቀሪ ውዝፍ ብድር ሲታይ ከእቅድ አንፃር ሲነፃፀር ወደ 211% ከፍ ሊል ችሏል።

- ✓ በቀሪ ውዝፍ ብድር በዚህ ዓመት ከፍተኛ ውዝፍ የሚታይባቸው የብድር አይነቶች በቅደም ተከተል የሴቶች ያለ ማስያዥ (Woc- Women's without collateral) (28,122%)፣ እሙን ደንበኛ (1,450%)፣ አውድ (321%) ፣ ተዘዋዋሪ (290%) ፣ 3 እግር ባጃጅ ብድር (244%)፣ ዋስትና ፈንድ (234%)፣ የቤት መስርያ (232%)፣ መደበኛ (231%)፣ገ/ፓኬጅ (224%) ሌሎች የመሳሰሉ ትላልቅ ቀሪ የብድር ውዝፎች ከእቅድ አንፃር የሚታይባቸው የብድር አይነቶች ናቸው። ከዚህ ዋና ዋና ምክንያቶች ተዘዋዋሪ ብድር ወጣቱ አብዛኛው ስራላይ ባለመኖሩ ፣ የብድር መስጠት ጥራት አለመኖሩ እና ሌሎችም የመሳሰሉት ሲሆኑ ይህ በቀጣይ ዓመት አስቀድሞ በመፈተሽ እና በማጥናት ያለን የብድር ውዝፍ የሚመለስበት ሁኔታ መፈጠር አለበት።

### 4.1.3. የብድር ውዝፍ ካለፈው በጀት ዓመት ሰነ 2014/15ዓ/ም ጋር ሲነፃፀር

- ✓ ባለፈው ዓመት ሰኔ የነበረን ውዝፍ 6.538 ቢልዮን ብር ሲሆን በዚህ አመት ያለን ውዘፍ ሲታይ 5.075 ቢልዮን ብር ሊሆን ችሏል። ከባለፈው ዓመት ሰኔ ጋር ሲነፃፀር የዚህ ዓመት በብር1.247 ቢልዮን ውዝፍ ሊቀንስ ችሏልዩ። ከዚህ በተጨማሪ በባለፈው ዓመት ሰኔ የውዝፍ ብዛት ውዝፍ ገብተው የነበሩ ተበዳሪዎች 355,122 የነበረ ሲሆን በዚህ ዓመት ወደ 212,608 ሊወርድ ችሏል። ይህ ማለት ውዝፍ ውስጥ ገብተው የነበሩ ተበዳሪዎች በ 142,514 ሰው ሊቀንስ ችሏል።
- ✓ በዚህ ዓመት የተሻለ የውዝፍ ቅናሽ ያሳዩ የብድር ዓይነቶች የወዴፕ (77%)፣ የሰራሕተኛ ብድር (70%) ፣ኤለክትሪክ (46%) ፣ ደሞወዝተኛ (30%) እንዲሁም ቢዝነስ (27%) በተነፃፃሪ የተሻለ የውዝፍ ቅናሽ ያሳዩ የብድር አይነቶች ናቸው ።

### 4.1.4. ቀሪ ብድር በሚመለከት

ሰንጠረዥ2፡- ቀሪ ብድር በጀት ዓመት2015/16 ከ ባለፈው በጀት ዓመት 2014/15 ጋር ሲነፃፀር

| ዓይነት | ሰኔ 2014/15 ዓ/ም መጠን ቀሪ ብድር በቢልዮን ብር | | 2015/16 ዓ/ም መጠን ቀሪ ብድር በቢልዮን ብር | |
|---|---|---|---|---|
| | በብር | ቀ/ተበዳሪ/ ብዛት | በብር | ቀ/ተበዳሪ/ ብዛት |
| እቅድ | 12.06 | 478,492 | 13.999 | 532,174 |
| ፍፃሜ | 9.954 | 335,186 | 10.95 | 246,463 |
| % | 83 | 70 | 78 | 46 |
| ከ 2014/15 ያለው ጭማሪ /ቀነስ | | | 0.996 | -88,723 |

- ✓ እንደ ተቋም ያለን ቀሪ ብድር መጠን እቅድ 13.999 ቢሊዮን ብር የነበረ ሲሆን ፍፃሜ ደግሞ ብር 10.950 ቢሊዮን ብር ቀሪ ብድር ሊሆን ችሏል ። የቀሪ ብድር መጠን ከ በጀት ዓመት 2014/15 ሲነፃፀር በ 0.996 ቢልዮን ብር ጭማሪ ሊያሳይ ችሏል። በሌላ በኩል ደግሞ ቀሪ በተበዳሪዎች ሲታይ እቅድ የሰው ብዛት

532,174 ሲሆን ፍፃሜ በሰው 246,463 ሲሆን ይህ ከበጀት ዓመት 2014/15 ሲነፃፀር በ 88,723 ሰው ሊቀንስ ችሏል፡፡ ስለዚህ በዚህ ዓመት በ 246,463 ደንበኞች እጅ ብር 10.950 ቢሊዮን እንዳለ የሚያሳይ ነው፡፡ በቀጣይ ዓመት በቀሪ ብድር ላይ በደንብ መስራት እንደሚያስፈልግ ያሳያል፡፡

### 4.1.5. ቁጠባ በሚመለከት

- ✓ በቁጠባ አገልግሎት በዚህ ዓመት አዲስ ቆጣቢዎች ብር 4 ቢሊዮን እንዲቀጥቡ እቅድ ተይዞ ፈፃሜ ብር 0.826 ቢልዩን ወይም ደግሞ 20.7% ከእቅዱ ሊፈፀም ተችሏል ፡፡ ይህ ከበጀት ዓመት 2014/15 የዓመት አፈፃፀም ሲነፃፀር በዚህ ዓመት ቁጠባ ፍፃሜ በ 2.28% የጨመረ ሲሆን ጠቅላላ ቁጠባ እንደተቋም ደግሞ በ6.31% ሊጨምር ችሏል፡፡ ስለዚህ በሚቀጥለው ዓመት ቆጣቢዎች የቆጠቡትን በብዛት የሚወስዱበት ያለ ምክንያት በደንብ ተጠንቶ ማስተካክያ ሊደረግበት ይገባል፡፡
- ✓ በቆጣቢዎች በኩል ሲታይ ደግሞ 100,000 እንዲቆጥቡ እቅድ ተይዞ ፍፃሜ ሲታይ 297,851 አዳዲስ ደንበኞች ሊኖሩን ችሏል፡፡ ይህ ከባለፈው 2014/15 በጀት ዓመት የቆጣቢዎች አፈፃፀም ሲነፃፀር በዚህ ዓመት በ290,443 ሊጨምር ችሏል፡፡ ጠቅላላ እንደ ተቋም ያሉን የቆጣቢዎች ብዛት በ 21.92% ሊጨምር ችሏል፡፡ በዚህ ዓመት በርከት ያለ የገቢ እና ወጪ እንቅስቃሴ ያለ መሆኑና በተለይ መንግስታዊ ያልሆነ ቁጠባ ፣ የቡድን ቁጠባ እና ተንቀሳቃሽ ቁጠባ በርከት ያለ ገንዘብ ወጪ እንዳደረጉ የሚያመላክት ሲሆን በሰው ኋይል ደግሞ በተለይ ከእድሜ በታች፣ የማይበደሩ እና ተበዳሪዎች፣ መንግስታዊና ግዜ ገደብ ቆጣቢዎች እየጨመረ እየሄደ ያለ መሆኑ የሚያመላክት ነው፡፡
- ✓ ስለሆነም በዚህ በጀት ዓመት ብር 7.796 ቢሊዮን የተሰበሰበ ሲሆን ብር 6.969 ቢሊዮን ደግሞ ወጪ ተደርጓል፡፡ ስለዚህ ለደንበኞች ሰፊ የቁጠባ እንቅስቃሴ የተደረገ መሆኑ ያሳያል፡፡
- ✓ እንደ ተቋም እስከአሁን የቆጣቢዎች ብዛት 1,656,966 የደረሱ ሲሆን የቆጠቡት መጠን ብር 13.915 ቢሎዮን ሊደርስ ችሏል፡፡

### 4.1.6. የዲጅታል አገልግሎት

- ✓ የቴሌ ብር ማንዋል ተዘጋጅቶ ወደ አገልግሎት እንዲውል ተደርጓል ፡፡
- ✓ በዚህ ዓመት በ155 ቅርንጫፎች የቴሌ ብር አገልግሎት ለመጀመር እቅድ ተይዞ በ 149 ቅርንጫፎች ስራ እንዲጀምሩ የተደረገ ሲሆን ይህ የእቅዱ 96% ሊፈፀም ችሏል፡፡
- ✓ በዚህ ዓመት በቴሌ ብር የተደረጉ የገንዘብ እንቅስቃሴዎች ሲታይ ገቢ ብር 65,443,683.84 የተደረገ ሲሆን በሰው ደግሞ 34,859 በወጪ በብር 3,200,665.06 ብሰው 33,931 ከወጪ ቀሪ ብር 62,243,018.78 በሰው 33,931 ከዚህ እንቅስቃሴ ወደ ተቋሙ ገቢ የተደረገ ኮሚሽን ደግሞ ብር 147,983.87 ሁኖ በዚህ ዓመት አዳዲስ 3,034 ደንበኞች ቴሌ ብር ተመዝግበዋል፡፡

### 4.1.7. የኤምብር አገልግሎት

- ✓ በ ኤምብር የነበሩ ችግሮች እንዲፈቱ በመቻላቸው ያልተወራረደ ሂሳብ የነበራቸው ለ 30 ኤጀንት ብር 730,000 እንዲከፈሉ ተደርጓል፡፡

### 4.1.8. ኢንሹራንስ በሚመለከት

- ✓ የህይወት መድን አገልግሎት (credit life insurance ) ብድር ከሚወስዱ ተበዳሪዎች ከ129,124 ደንበኞች ብር 79,181,056 ክፍያ/premium / ለመሰንሰብ እቅድ ተይዞ ፍፀሜው ሲታይ ደግሞ ብር 67,531,348.13 ይሆናል በሰው ብዛት ደግሞ 104,369 ሊሆን ችሏል ።
- ✓ የካሳ ክፍያ 160 ለሚሆኑ ተበዳሪ ደንበኞች በሞት ለተለዩ ብር 4,800,000 **ካሳ ለመክፈል እቅድ ተይዞ ከዚህ ለ** 128 ደንበኞች ብር 3,087,426.20 የህይወት መድን የብድር ካሳ ተከፍሏል፡፡
- ✓ የሰራተኞች የህይወት መድን (self–staff life insurance) በእቅድ ደረጃ ለአካል ጉዳተኞች 24 ፣ ሞት 80 በድምር ለ104 ሰራተኞች ጉዳት ለደረሰባቸው ሰራተኞች ብር 600,000 በሞት ለተለዩ ሰራሕተኞች 9,400,000 ብር በድምር ብር 10,000,000 ለሰራተኞች መድን ዋስትና የተያዘ ሁኖ ፍፃሜው የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ሰራተኞች ብዛት 2 ሰው ብር 227,980.80 ተከፍሏል ፤ በሞት ለተለዩ ብዛት 4 ሰው ብር 1,399,560 ተከፍሏል። በአጠቃላይ ለ 6 ሰው ብር 1,627,540.80 ለሰራተኞች የተከፈለ ካሳ ነው፡፡

## 4.2. የኣይቲና የ ኮር ባንኪንግ ሲስተም መደቦች ማስፋፋት አፈፃፀም በተመለከተ

### 4.2.1. የኮር ባንኪንግ ሲስተም ቴክኒካል ድጋፍ በተመለከተ

- ✓ የቀንተቀን የሲስተም ኣድሚኒስትሬሽን ስራዎች ኮፒ፣ባክ ኣፕ (backup) በየግዜው በስርአት እንዲሰራ ተደርጓል፡፡
- ✓ ለዩዘር ተጠቃሚዎች መከታተል ፣ በዩዘር የሚያጋጥሙ የፓስዎርድ መጥፋት ማስተካከያዎች ፣ አዳዲስ የዘሮች መፍጣር
- ✓ የ 20 ንኡስ ቅርንጫፍ ላይቭ ለመሆን የሚያስፈልጉ ዳታዎች በመዘጋጀትወደ ላይቭ ሲስተም እንዲገቡ ተደርጓል፡፡

### 4.2.2. የአይቲ ኢንፍራስትራክቸርና ድጋፍና ክትትል

- ✓ በብሄራዊ ባንክ መመርያ መሰረት የኢንፎርሜሽን ሰኲዩሪቲ ጋቨርናንስ አሰራር ፣ የዳታ ሰንተር ኣክሰስ ፖሊሲና ፕሮሲጀር ፣ የሃብት መመዝገብያ (Asset Registration) ዶክመንት ፣ የኔትዎርክና ሌሎች የሌክትሮኒክስ ማተርያሎች ያለ ኮንፊገሬሽን የሚሉ ማንዋሎች ተዘጋጅተው ወደ ስራ እንዲ ገቡ መደረጋቸው ፡፡

### 4.2.3. የአይቲ ሰክዩሪቲ ስራዎች በሚመለከት

- ✓ በኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ በተሰጠ መመርያ መሰረት የስታንዳርድ ፖሊሲ ማርቀቅ በዶክመንት እንዲዘጋጅ ተደርጓል።
- ✓ በዳታ ሰንተር ሪስክ ኣሰስመንት ተሰርቶ ወደሚመለከተው እንዲላክ ተደርጓል፡፡
- ✓ የሳይበር ሰኩሪቲ ትምህርትና ስልጠና የሚመለከት ዶክመንት በ'ድራፍት' መልክ እንዲዘጋጅ ተደርጓል።

## 4.3. የኮርፖሬት ሰርቪስ መደቦች አፈፃፀም

### 4.3.1. ፋይናንስ በሚመለከት

- ✓ ሰራተኛው በየቀኑ ለሚሰራቸው ስራዎች እንደ አበል፣ ደሞዝ እና ጥቅማጥቅሞች፣ ፣ቢዝነስ ኣድቫንስ፣ ብድር፣ የዓመት ዕረፍት፣ አክቲንግን ትራንስፖርትና አለዋንስ ድህረ ክፍያዎች እና ሌሎች ክፍያዎች ተከፍለዋል።
- ✓ በዋና ቢሮ ውስጥ የነበረ ዲቶ/አሮጌ እና የተቀደደ/ ገንዘብ ከአንድ ሚልዮን በላይ ወደ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ገቢ ተደርጓል።
- ✓ ያለፈው የ2021-2023 ፋይናንሻል ሪፖርት በውጭ ኦዲተር ኦዲት ተደርጓል ፡

ሰንጠረዥ1፡- ሀብትና እዳ በሚመለከት

| ዓይነት | ሰኔ 2014/15 ዓ/ም በቢልዮን | | ሰኔ 2015/16 በቢሊዮን | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | እቅድ | ፍፃሜ | እቅድ | ፍፃሜ | ከ2014/15 ያለው ቀነስ/ ጭማሪ |
| ጠ/ሀብት | 15.734 | 18.752 | 15.571 | 11.968 | -6.784 |
| ዕዳ | 14.157 | 14.472 | 18.246 | 16.251 | 1.779 |
| ካፒታል | 1.577 | -3.647 | -2.675 | -4.283 | -0.636 |
| ጥሬ ገንዘብ | 2.717 | 3.516 | 3.773 | 2.57 | -0.946 |
| ጠ/ቁጠባ | 12.586 | 13.089 | 13.089 | 13.915 | 0.826 |

- ✓ እንደ ተቋም በዚህ በጀት ዓመት ጠቅላላ ሃብት ብር 15.571 ቢልዮን **እንዲሆን እቅድ ተይዞ በዚህ ዓመት** ብር 11.968 ቢልዮን **ሊፈፀም ችሏል**። ይህ ካለፈው በጀት ዓመት 2014/15 አፈፃፀም ሲነፃፀር የተቋማችን ጠቅላላ ሃብት በብር 6.784 ቢልዮን ቅናሽ ሊሳይ እኋል።
- ✓ ዕዳ በዚህ በጀት ዓመት ብር 18.246 ቢልዮን **እንዲኖረን እቅድ ተይዞ** ፋፃሜ ብር 16.251 ቢልዮን ዕዳ ሊኖረን ችሏል ። ይህ ከ በጀት ዓመት 2014/15 አፈፃፀም ሲነፃፀር በብር 1.779 ቢልዮን በዚህ ዓመት የእዳ መጠን ሊጨምር ችሏል።

- ✓ ካፒታል በዚህ በጀት ዓመት ብር (2.675) ቢልዮን እንዲሆን እቅድ ተይዞ ፍፃሜ ብር (4.283) ቢልዮን ሊሆን ችሏል ። ይህ ከሰኔ ወር 2014/15 ዓ/ም አፈፃፀም ሲነፃፀር የካፒታል መጠን በብር 0.636 ቢልዮን ሊቀንስ ችሏል።
- ✓ በእጅ እና በባንክ ያለው ጥሬ ገንዘብ እቅድ ብር 3.773 ቢሊዮን ሲሆን ፍፃሜ ብር 2.570 ቢሊዩን ሊሆን ችሏል። ይህ ካለፈው አመት 2014/15 ዓ/ም ጋር ሲነፃፀር በዚህ ዓመት ጥሬ ገንዘብ በብር 0.946 ቢልዮን ሊቀንስ ችሏል።
- ✓ በሌላ በኩል ጠቅላላ ቁጠባ ከባለፈው በጀት ዓመት 2014/15 ጋር ሲነፃፀር በብር 0.826 ቢሊዮን ሊጨምር ችሏል።

**ሰንጠረዥ2. የሃብት እና እዳ መግለጫ (ሰነ 30, 2024 ዓ/ም/ፈ)**

| **የሃብት ዓይነት** | **መጠን/በቢሊዮን/** | **ድርሻ በ%** |
|---|---|---|
| ጥሬ ገንዘብ እና በባንክ ያለ ገንዘብ | 2,570.24 | 21.48% |
| የሚሰበሰብ ብድር /የተጣራ/ | 5,399.54 | 50.11% |
| ተሰብሳቢ ገንዘብ | 2,461.10 | 15.57% |
| አላቂ የቢሮ እቃዎች | 51.83 | 0.43% |
| ቋሚ እቃዎች/የተጣራ/ | 389.64 | 3.26% |
| ኢንቨስትመንት | 151 | 1.26% |
| ሌሎች | 944.66 | 7.89% |
| **ድምር** | 11,968.01 | **100%** |

**ሰንጠረዥ3፡- እንደ ተቋም ያለን ሃብት ምንጩ ሲታይ**

| **ዓይነት ፍልፍል** | **መጠን/በሚሊዮን/** | **በመቶኛ ¼%¼** |
|---|---|---|
| ቁጠባ | 13,915.87 | 116.28% |
| ብድር/ከባንክ/ | 697.59 | 5.83% |
| በማረት ቀጥታ የገባ | 131.56 | 1.10% |
| የተከፈለ ካፒታል ካፒታል | 10 | 0.08% |
| ትርፍ | -4,283.73 | -35.79% |
| ማቺንግ ፈንድ | 2.49 | 0.02% |
| ሌሎች | 1,494.23 | 12.49% |
| ድምር | **11,968.01** | 100% |

## 5. እንደ ተቋም የነበረን ጥንካሬ እና ድክመት

### 5.1. ጥንካሬ

- በዚህ አመት የተሰጠ ብድር የተሻለ ጥራት ያለው መሆኑ
- ተቋማችን ባደረገው የወለድ ምህረት ብድር እንዲ መለሰ በር የከፈተ መሆኑ
- አሁን ያለው ዲጂታል ቴክኖሎጂ የት እንደደረሰ ለማየት ተሞክሮ በማምጣት ወደ ተግባር ለማስገባት ከ ኮኦፐረቲብ ባንክ በተደረገ ንግግር መሰረት ትልቅ ተሞክሮ ሊገኝ መቻሉ
- ተቋርጦ የነበረው የኮርባንኪንግ ሲስተም የማስፋፋት ስራዎች እንደገና ወደስራ እኒመለስ ብዙ ጥሮቶች መደረጋቸው
- ተቋሙ የራሱ ዌብ ሳይት እንዲነኖሮው መደረጉ

### 5.1.2. በድክመት የሚታይ

- የብድር መስጠት መቆሙ ለብድር መመለስ ትልቅ እንቅፋት መሆኑ
- አንዳአንድ ደንበኞች ጠቅላላ ወለድ ምህረት እንዲደረግለት መፈለግ፣
- የ CRB(credit reference bureau) ሪፖርትና ወራዊው ሪፖርት በሲስተም አለመስራት
- ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ሪፖርት በወቅቱ አለመላክ

### 5.1.3. መፍትሄ ሐሳቦች

- ✓ በሲስተም ላይ ያለ ክፍተት ማስተካከል፡፡
- ✓ የኤፒአይ ስራ ከ ኮርባንኪንግ ፓርትነር ከብዙ ድርድር በኋላ ስራ እንዲጀምሩ መደረጉ
- ✓ ኣናሊቲክስ ስራ በመስራት፣ሰኩዩሪቲ ዲቫይስ በማግባት እና አይቲ ጋቨርናንስ ዶክመንታት ወደ ስራ በፍጥነት እንዲገባ ማድረግ፡፡

## 5. ለቀጣይ ትኩረት የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች

- ተቋሙ የሚፈልጋቸው አዳዲስ አሰራሮች የሚሰሩ የበቁ ባለሙያዎች ማሰልጠን እና ማፍራት
- በቀጣይ ሰፊ የብድር ማስመለስ እና ቁጠባ መሰብሰብ ስራዎች እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡
- ለባንክ ሽግግር እና ለኢንሹራንስ ሽግግር ሰይስተም ማሻሻል (System upgrading) በፕሮጀክት መልክ የሚያስፈልግ የሰው ሃይል እና ማተርያል በማሟላት ይሰራል፡፡
- ወደ ሲስተም ያልገቡ ቅርንጫፎች እና ንኡስ ቅርንጫፎች የሚያስፈልግ ኢንፍራስትራክቸር ከሚመለከታቸው አካላት በመግባባት እና በመስራት ወደ ስራ መግባት፡፡

- የተለያዩ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች እንደ አጭር መልእክት ማስተላለፍያ (SMS notification) ሞባይል ባንኪንግ፣ ኢንቴረኔተ ባንኪንግ፣ ሞባይል ዋሌትና ኢኣርፒ (ERP) የመሳሰሉትን ወደ ስራ እንዲገቡ በትኩረት መስራት ።

| 1. እቅድ እና ፍፃሜ ሰኔ 2024 ብድር | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተ/ቁ | የብድሩ ዓይነት | ግብ | | ፍፃሜ | | % | |
| | | ሰው | ገንዘብ | ሰው | ገንዘብ | ሰው | ገንዘብ |
| 1 | መደበኛ | 37,709 | 1,125,339,627 | **18,318** | **1,554,752,292.00** | 48.58 | 138.16 |
| 2 | ደሞዝተኛ | 9,953 | 296,758,648 | **1,644** | **167,280,576.00** | 16.52 | 56.37 |
| 3 | ቲቪቲ | | - | **-** | **-** | - | - |
| 4 | ሕ/ስ/ማ | - | - | **-** | **-** | - | - |
| 5 | ግብአቶች | | - | **-** | **-** | - | - |
| 6 | ገ/ፓኬጅ | 41,580 | 1,239,749,280 | **490** | **11,531,143.50** | 1.18 | 0.93 |
| 7 | ከ/ፓኬጅ | 31,680 | 944,570,880 | **1,290** | **31,860,007.69** | 4.07 | 3.37 |
| 8 | ዋስትና ፈንድ | 2,274 | 67,801,584 | **2** | **300,000.00** | 0.09 | 0.44 |
| 9 | 3 እግር ባጃጅ ብድር | 1,100 | 32,797,600 | **3** | **1,100,000.00** | 0.27 | 3.35 |
| 10 | ተዘዋዋሪ | | - | **14** | **2,000,000.00** | - | - |
| 11 | ዌዴብ | 1,290 | 645,000,000 | **33** | **20,004,000.00** | 2.56 | 3.1 |
| 12 | ሞዴልንና ተሸጋጋሪዎች | 90 | 15,479,917 | **6** | **2,600,000.00** | 6.67 | 16.8 |
| 13 | ቢዝነስ | 4,089 | 703,304,237 | **2,022** | **1,327,216,200.00** | 49.45 | 188.71 |
| 14 | ቤት መቅርያ | 9,431 | 1,622,123,321 | **1,005** | **431,706,643.11** | 10.66 | 26.61 |
| 15 | ኤለክትሪክ | - | - | **-** | **-** | - | - |
| 16 | ዱቤ | 900 | 26,834,593 | **85** | **32,363,547.76** | 9.44 | 120.6 |
| 17 | ሊዝ | - | - | **-** | **-** | - | - |
| 18 | ሀይል ቆጣቢ | 1,208 | 36,017,728 | **11** | **1,250,000.00** | 0.91 | 3.47 |
| 19 | የሰራተኛ ብድር | 320 | 55,039,705 | **1,324** | **203,901,268.16** | 413.75 | 370.46 |
| 20 | ታማኝ ታማኝ | 1,180 | 35,182,880 | **1,167** | **177,344,900.00** | 98.9 | 504.07 |
| 21 | WOC | 1,540 | 154,000,000 | **79** | **19,947,800.00** | 5.13 | 12.95 |
| 22 | Tech .Mult | | | **-** | **-** | - | - |

| | ድምር | 144,344 | 7,000,000,000 | **27,493** | **3,985,158,378** | 19.05 | 56.93 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|

| የብድር እና ውዝፍ ማስመለስ አፈፃፀም (በብር) | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ሰኔ ወር 2016 ዓ/ም /2024 ዓ/ፈ | | | | | | | |
| ተ/ቁ | የብድር ዓይነት | የብድር አመላለስ | | | ቀሪ ውዝፍ | | |
| | | እቅድ | ፍፃሜ | በ% ፍፃሜ | እቅድ | ፍፃሜ | በ% ፍፃሜ |
| 1 | መደበኛ | 436,653,162 | 565,736,056 | 129.56 | 438,026,261 | 1,012,485,085 | 231.15 |
| 2 | ደመወዝተኛ | 75,069,667 | 107,854,041 | 143.67 | 78,974,477 | 149,819,064 | 189.71 |
| 3 | ቲቪቲ | - | - | | 237,798 | - | - |
| 4 | ሕ/ስ/ማ | - | - | | 757,092 | 100,260 | 13.24 |
| 5 | ግብኣቶች | - | - | | 1,683,577 | 2,060,653 | 122.40 |
| 6 | ገ/ፓኬጅ | 226,640,519 | 154,668,315 | 68.24 | 245,448,787 | 549,811,066 | 224.00 |
| 7 | ከ/ፓኬጅ | 244,672,696 | 206,246,065 | 84.29 | 257,480,384 | 538,123,282 | 209.00 |
| 8 | ዋስትና ፈንድ | 131,072,222 | 91,114,141 | 69.51 | 139,860,734 | 327,359,227 | 234.06 |
| 9 | 3 እግር ባጃጅ ብድር | 23,246,399 | 17,178,163 | 73.90 | 22,935,827 | 56,037,433 | 244.32 |
| 10 | ተዘዋዋሪ | 153,676,409 | 9,930,186 | 6.46 | 163,786,734 | 474,543,303 | 289.73 |
| 11 | ዌዴፕ | 13,226,067 | 25,843,936 | 195.40 | 19,382,594 | 9,064,987 | 46.77 |
| 12 | ሞዴልና ተሸጋጋሪ | 26,096,471 | 18,542,339 | 71.05 | 31,903,089 | 65,496,019 | 205.30 |
| 13 | ቢዝነስ | 514,935,836 | 665,383,415 | 129.22 | 603,006,405 | 1,176,150,660 | 195.05 |
| 14 | ቤት መስርያ | 1,101,356,274 | 997,967,802 | 90.61 | 376,867,350 | 877,514,549 | 232.84 |
| 15 | ኤሌክትሪክ | - | 6,051,108 | - | - | 7,081,009 | - |
| 16 | ዱቤ /አውድ/ | | | | | | |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 6,685,573 | 3,000,609 | 44.88 | 2,310,968 | 7,421,030 | 321.12 |
| 17 | ሊዝ | - | 2,190,973 | - | 4,990,256 | 10,928,769 | 219.00 |
| 18 | ሃይል ቆጣቢ | 3,401,692 | 2,864,379 | 84.20 | 3,499,381 | 7,141,219 | 204.07 |
| 19 | የሰራተኛ ብድር | 43,129,839 | 67,289,226 | 156.02 | 13,197,237 | 10,294,409 | 78.00 |
| 20 | እሙን ደንበኛ | 90,008 | 30,482,409 | 33,866.47 | 80,776 | 1,171,550 | 1,450.38 |
| 21 | Woc | 47,165 | 4,661,026 | 9,882.34 | 29,870 | 8,400,082 | 28,122.43 |
| 22 | Techno. Multipli | | - | - | | 35,765 | - |
| | **ድምር** | **3,000,000,000** | **2,977,004,188** | 99.23 | **2,404,459,595** | **5,291,039,419** | **220.05** |

| የውዝፍ ንፅፅር | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ሰኔ ወር 2016 ዓ/ም /2024 ዓ/ፈ | | | | | | | |
| ተ/ቁ | የብድር ዓይነት | ሰኔ 2023 የነበረ ውዝፍ | | ሰኔ 2024 የነበረ ውዝፍ | | ጭማሪ/ቀነስ ውዝፍ | |
| | | የተበዳሪዎች ብዛት | የገንዘብ መጠን | የተበዳዎች ብዛት | የ ገንዘብ መጠን | የተበዳሪዎች ብዛት | የገንዘብ መጠን |
| 1 | መደበኛ | 76,334 | 1,199,973,983.31 | 68,484 | 1,012,485,085.00 | -7,850 | -187,488,898 |
| 2 | ደሞዝተኛ | 13,174 | 214,419,551.60 | 9,802 | 149,819,063.82 | -3,372 | -64,600,488 |
| 3 | ቲቪቲ | 180 | 633,394.09 | - | - | -180 | -633,394 |
| 4 | ሕ/ስ/ማ | 264 | 2,016,570.82 | 14 | 100,259.55 | -250 | -1,916,311 |
| 5 | ግብአቶች | 75,828 | 4,484,335.18 | 42,533 | 2,060,652.54 | -33,295 | -2,423,683 |
| 6 | ገ/ፓኬጅ | 93,602 | 651,759,105.33 | 76,001 | 549,811,065.61 | -17,601 | -101,948,040 |
| 7 | ከ/ፓኬጅ | 36,713 | 694,590,627.74 | 26,613 | 538,123,281.88 | -10,100 | -156,467,346 |
| 8 | ዋስትና ፈንድ | 5,799 | 380,050,938.33 | 4,357 | 327,359,227.45 | -1,442 | -52,691,711 |
| 9 | 3 የእግር ባጃጅ ብድር | 606 | 68,243,961.35 | 438 | 56,037,433.18 | -168 | -12,206,528 |
| 10 | ተዘዋዋሪ | 3,980 | 456,282,672.11 | 3,124 | 474,543,303.26 | -856 | 18,260,631 |
| 11 | ዌዴፕ | 288 | 40,472,580.99 | 76 | 9,064,987.25 | -212 | -31,407,594 |
| 12 | ሞዴልና ተሻጋጋሪዎች | 240 | 85,037,367.10 | 181 | 65,496,019.31 | -59 | -19,541,348 |
| 13 | ቢዝነስ | 6,331 | | | | -1,942 | -438,052,322 |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1,614,202,981.94 | 4,389 | 1,176,150,660.03 | | |
| 14 | የቤት መስርያ | 37,219 | 1,048,782,244.35 | 27,840 | 877,514,548.80 | -9,379 | -171,267,696 |
| 15 | ኤሌክትሪክ | 24 | 13,132,117.16 | 13 | 7,081,008.69 | -11 | -6,051,108 |
| 16 | ዱቤ | 196 | 6,604,733.38 | 199 | 7,421,029.51 | 3 | 816,296 |
| 17 | ሊዝ | 152 | 13,271,995.38 | 144 | 10,928,768.70 | -8 | -2,343,227 |
| 18 | ሃይል ቆጣቢ | 2,637 | 9,235,610.45 | 1,851 | 7,141,218.98 | -786 | -2,094,391 |
| 19 | የሰራተኛ ብድር | 1,552 | 34,560,855.82 | 729 | 10,294,409.07 | -823 | -24,266,447 |
| 20 | እሙን ደንበኛ | 2 | 232,323.72 | 459 | 1,171,550.33 | 457 | 939,227 |
| 21 | Woc | 1 | 88,187.26 | 80 | 8,400,081.85 | 79 | 8,311,895 |
| 22 | Techno. Multipl | | | 4 | 35,764.55 | | |
| | ድምር | 355,122 | 6,538,076,137 | 267,331 | 5,291,039,419 | -87,795 | -1,247,072,483 |

| ቀሪ ብድር | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ሰኔ ወር 2016 ዓ/ም /2024 ዓ/ፈ | | | | | | | |
| ተ/ቁ | የብድር ዓይነት | የቀሪ ብድር ብዛት | | | የቀሪ ብድር መጠን መጠን | | |
| | | እቅድ | ፍፃሜ | ብ% ፍፃሜ | እቅድ | ፍፃሜ | ብ% ፍፃሜ |
| 1 | መደበኛ | 122,628 | 87,647 | 71.47 | 2,140,073,541 | 2,661,791,567 | 124.38 |
| 2 | ደሞዝተኛ | 25,211 | 11,688 | 46.36 | 471,902,977 | 306,813,746 | 65.02 |
| 3 | ቲቪቲ | 180 | - | - | 633,394 | - | - |
| 4 | ሕ/ስ/ማ | 264 | 14 | 5.30 | 2,016,571 | 100,260 | 4.97 |
| 5 | ግብአቶች | 75,828 | 42,533 | 56.09 | 4,484,335 | 2,060,653 | 45.95 |
| 6 | ገ/ፓኬጅ | 139,041 | 80,341 | 57.78 | 1,768,613,075 | 600,456,989 | 33.95 |
| 7 | ከ/ፓኬጅ | 71,568 | 29,112 | 40.68 | 1,515,504,656 | 623,882,965 | 41.17 |
| 8 | ዋስትና ፈንድ | 8,584 | 4,482 | 52.21 | 373,649,708 | 350,193,718 | 93.72 |
| 9 | የ3 እግሪ ባጃጅ ብድር | 1,754 | 446 | 25.43 | 87,037,625 | 57,949,713 | 66.58 |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 10 | ተዘዋዋሪ | 6,738 | 3,525 | 52.32 | 358,534,835 | 503,652,272 | 140.48 |
| 11 | ዌዴፕ | 14,300 | 144 | 1.01 | 675,862,483 | 27,664,204 | 4.09 |
| 12 | ሞዴልና ተሸጋጋሪዎች | 366 | 189 | 51.64 | 76,369,104 | 68,466,055 | 89.65 |
| 13 | ቢዝነስ | 9,781 | 5,585 | 57.10 | 1,905,122,788 | 2,384,412,733 | 125.16 |
| 14 | ቤት መስርያ | 44,572 | 29,057 | 65.19 | 4,187,743,514 | 3,060,220,319 | 73.08 |
| 15 | ኤሌክትሪክ | - | 13 | - | - | 7,081,009 | - |
| 16 | ዱቤ | 1,924 | 1,070 | 55.61 | 42,432,372 | 46,168,343 | 108.80 |
| 17 | ሊዝ | - | 144 | - | - | 10,928,769 | - |
| 18 | ሃይል ቆጣቢ | 4,044 | 1,896 | 46.88 | 43,954,047 | 9,236,276 | 21.01 |
| 19 | የሰራተኛ ብድር | 2,668 | 2,097 | 78.60 | 155,713,802 | 269,834,944 | 173.29 |
| 20 | እሙን ደንበኛ | 1,182 | 1,127 | 95.35 | 35,392,872 | 153,465,034 | 433.60 |
| 21 | Woc | 1,541 | 116 | 7.53 | 154,110,039 | 22,024,309 | 14.29 |
| 22 | Techno. Multipli | | - | | | 35,765 | - |
| | ድምር | 532,174 | 301,226 | 56.60 | 13,999,151,739 | 11,166,439,642 | 79.77 |

**Comparison of Budget & Actual**

**Balance sheet**

**Period July 1, 2023 – June 30, 2024**

| Description | Budget | Actual | Actual-Budget Variance | Remark |
|---|---|---|---|---|
| **ASSETS** | | | | |
| Current Assets: | | | | |
| Cash | 3,773,100,126.53 | 2,570,240,270.85 | (1,202,859,855.68) | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| Staff debtor | 14,105,264.05 | 105,438,205.19 | 91,332,941.14 | |
| Loans & Advance | 10,584,050,748.11 | 10,950,934,041.15 | 366,883,293 | |
| Allow. For bad debts | (1,239,780,908.41) | (5,551,392,188.10) | (4,311,611,279.69) | |
| Investment | 150,999,900.00 | 151,000,083.25 | 183.25 | |
| A/receivable | 1,855,231,568.63 | 2,461,199,196.4 | 7,812,405.78 | |
| Ethio telecom E-money Depositer | 0.00 | 118,568.88 | 118,568.88 | |
| Migration acc | 0.00 | 39,215,314.82 | 39,215,314.82 | |
| Pre- payment | 31,566,529.70 | 75,742,125.80 | 44,175,596.10 | |
| Other than fixed & supplies | 6,323,018.76 | 19,928,079.90 | 13,605,061.14 | |
| Office supplies | 25,020,976.00 | 31,904,100.94 | 6,883,124.94 | |
| Adjustment & refund | 0.00 | 721,788,959.11 | 721,788,959.11 | |
| Gold | 0.00 | 339,221.34 | 339,221.34 | |
| Others | 0.00 | 2,009,560.88 | 2,009.560.88 | |
| **Total Current Assets** | **15,200,617,223.37** | **11,578,365,540.70** | | |
| Fixed Assets | | | | |
| Office furniture | 86,428,211.00 | 128,239,141.16 | 41,810,930.16 | |
| Office equipment | 27,463,162.35 | 28,951,799.43 | 1,488,637.00 | |
| Motor vehicle | 68,004,216.03 | 52,710,415.11 | (15,293,800.92) | |
| Computer | 78,576,594.04 | 124,302,505.90 | 45,725,911.86 | |
| Softwear & network | 163,940,740.55 | 170,547,564.26 | 6,606,823.71) | |
| Building | 296,929,341.39 | 247,933,716.88 | (48,995,624.51) | |
| (Accumulated Dep.) | (350,468,402.97) | (363,042,052.68) | (12,573,649.71) | |
| **Net Fixed Assets** | **370,873,862.39** | **389,643,090.06** | **18,769,227.67** | |
| **TOTAL ASSETS** | **15,571,491,085.76** | **11,968,008,630.76** | **(3,603,482,455.00)** | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| **LIABILITIES** | | | | |
| Premium Payable | 0.00 | 56,943,210.44 | 56,943,210.44 | |
| Current account | 4,260,248,301.95 | 656,747,700.38 | (3,603,500,601.57) | |
| Personal savings | 11,990,982,416.50 | 12,654,660,148.10 | 663,677,731.60 | |
| Group savings | 392,240,530.20 | 503,169,700.60 | 110,929,170.40 | |
| Center savings | 22,909,010.35 | 22,745,973.42 | (163,036.93) | |
| Time deposit | 9,847,222.74 | 78,543,782.72 | 68,696,559.98 | |
| Other payable | 756,079,428.50 | 941,932,444.54 | 185,853,016.04 | |
| A/payable | 437,651,922.81 | 614,248,448.65 | 176,596,525.84 | |
| A/payable S/branch | 50,305,739.09 | 7,931,561.01 | (42,374,178.08) | |
| Adjustment & refund | 0.00 | 17,222,471.97 | 17,222,471.97 | |
| Long term loan | 326,636,409.08 | 697,591,448.54 | 370,955,039.46 | |
| **TOTAL LIABILITIES** | **18,246,900,981.22** | **16,251,736,890.37** | **(1,995,164,090.85)** | |
| **Capital** | | | | |
| **Donation Capital Prior Year** | 131,564,141.64 | 131,564,141.64 | 0.00 | |
| **Paid up Capital** | 10,000,000.00 | 10,000,000.00 | 0.00 | |
| Prior year retained earnings | (2,786,961,564.19) | (5,722,342,412.49) | (2,935,380,848.30) | |
| Net income(Loss) | (30,012,472.91) | 1,297,050,011.24 | 1,327,062,4849.15 | |
| Total capital | **(2,675,409,895.46)** | **(4,283,728,259.61)** | (1,608,318,364.15) | |
| **Total Liab. & Capital** | **15,571,491,085.76** | **11,968,008,630.76** | **(3,603,482,455.00)** | |

| **Comparison of Income statement** | | | | |
|---|---|---|---|---|
| **Period July 1, 2023– June 30, 2024** | | | | |
| | | | **Actual-Budget** | |
| **Description** | **Budget** | **Actual** | **(Variance)** | **Remark** |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| **FINANCIAL INCOME:** | | | | |
| Int.earned on loan | 893,046,536.33 | 1,710,852,844.97 | 817,806,308.64 | Favorable |
| int. earned on deposit | 380,145,052.28 | 185,839,368.19 | (194,305,684.09) | Unfavorable |
| Donation Income | 0.00 | 0.00 | 0.00 | |
| **Service Revenue:** | | | | |
| Pension &Social Affair Service | 15,903.35 | 173,802.28 | 157,898.93 | F |
| Commission income | 823,347.04 | 1,173,016.96 | 349,669.92 | F |
| Telephone &Tell Birr | 9,563,004.81 | 233,958.224 | (9,329,046.57) | UN F |
| Estimation & Inspection Fees | 133,161.04 | 2,098,557.75 | 1,965,396.71 | F |
| **Other Income** : | | | | |
| Cash surplus | 100,000.00 | 1,124,199.61 | 1,024,199.61 | F |
| Sales of pass book | 337,926.33 | 2,416,316.75 | 2,078,390.42 | F |
| Penality | 79,182.90 | 156,239.34 | 77,056.44 | F |
| Sales of bid bond | 5,353,374.88 | 49,906.24 | (5,303,468.64) | UN F |
| Disposal of old asset | 20,123.00 | 79,041.38 | 58,918.38 | F |
| Office rent | 2,656,695.28 | 10,552,601.19 | 2,895,905.91 | F |
| Sales of Cheque | 30,552.80 | 27,548.00 | (3,004.80) | UNF |
| Discount | (546,024,414.09) | (157,910,614.71) | 388,113,799.38 | F |
| Sundries | 14,140,691.11 | 6,785,305.42 | (7,355,385.69) | UN F |
| **Total Financial Income** | **1,852,469,965.24** | **1,763,652,091.61** | **(88,817,873.63)** | UN F |
| **FINANCIAL COSTS:** | | | | |
| Interest Personal savings | 824,883,300.87 | 1,028,147,510.16 | 203,264,209.29 | F |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| Interest paid to Group savings | 13,671,947.29 | 15,687,356.97 | 2,015,409.68 | F |
| Interest paid to Center savings | 1,507,072.36 | 1,389,115.76 | (117,956.60) | F |
| Interest paid on borrowing | 59,905,289.51 | 186,093,089.12 | 126,187,799.61 | F |
| Premium Deposit Insurance | | 38,574,700.00 | 38,574,700.00 | F |
| **Total Financial Costs** | **903,704,420.16** | **1,269,891,772.01** | 366,187,351.85 | F |
| **Salaries & benefits** | | | | |
| Clerical & Non Clerical Staff salary | 254,135,352.00 | 483,223,281.51 | 229,087,929.51 | F |
| Cash Indemnity Allowance | 1,612,800.00 | 1,152,196.48 | (460,603.52) | F |
| Medical | 21,848,000.00 | 10,579,142.75 | (11,268,857.25) | F |
| Training & workshop | 17,143,140.00 | 931,363.97 | (16,211,776.03) | UNF |
| Reward & Prize | 25,049,543.00 | 512,261.33 | (24,537,281.67) | UNF |
| Education | 600,000.00 | 1,134,819.20 | 534,819.20 | F |
| Provident fund 12%&7% | 31,751,341.92 | 54,577,451.09 | 22,826,109.17 | F |
| Hardship allowance | 9,513,631.92 | 11,315,312.40 | 1,801,680.48 | F |
| Uniform | 22,562,392.25 | 5,482,877.05 | (17,079,515.20) | UNF |
| Acting Allowance | 2,400,000.00 | 10,672,383.67 | 8,272,383.67 | F |
| Transportation allowance | 30,502,800.00 | 19,397,504.73 | (11,105,295.27) | UNF |
| **Total Salaries & benefits** | **335,534,365.09** | **598,978,594.18** | **263,444,229.09** | F |
| | | | | |

| Description | Budget | Actual | Actual-Budget (Variance) | Remark |
|---|---|---|---|---|
| **General Expenses** | | | | |
| Legal fee | 672,250.00 | 539,797.20 | (132,452.80) | UNF |
| Audit fee | 550,000.00 | 494,500.00 | (55,500.00) | F |
| Advertisment & Promotion | 5,530,000.00 | 12,905,412.55 | 7,375,412.55 | F |
| Cleaning supply | 1,067,400.00 | 619,531.08 | (447,868.92) | UNF |
| Entertainment | 3,000,000.00 | 3,057,025.45 | 57,025.45 | F |
| Inauguration & anniversary | 1,350,000.00 | 1,262,878.11 | (87,121.89) | UNF |
| Moter Insurance | 650,000.00 | 326,863.76 | (323,136.24) | UNF |
| Maint.& rep. Equip, furniture | 616,400.00 | 1,010,544.24 | 394,144.24) | F |
| Main. & rep. Building | 3,245,000.28 | 1,740,569.73 | (1,504,430.55) | UNF |
| Main. & rep. Motor Veh. Computer | 4,442,000.00 | 1,730,395.59 | (2,711,604.41) | UNF |
| Perdiem & traveling | 4,837,764.56 | 24,154,723.42 | 19,316,958.86 | F |
| Petrol & Oil | 4,183,500.00 | 4,857,036.03 | 673,536.03 | F |
| Stationary & Printing | 4,788,644.50 | 20,642,278.67 | 15,853,634.17 | F |
| Postal Service | 120,000.00 | 41,137.90 | (78,862.10) | UNF |
| Office rent | 10,023,826.56 | 29,004,820.65 | 18,980,994.09 | F |
| Subscription | 502,420.09 | 1,693,715.69 | 1,191,295.60 | F |
| Sundries | 1,677,147.18 | 9,538,773.54 | 7,861,626.36 | F |
| Tel. Teleg. & Telex | 1,200,000.00 | 4,551,683.96 | 3,351,683.96 | F |
| Wages | 180,000.00 | 1,510,726.40 | 1,330,726.40) | F |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| Water & Light | 372,000.00 | 1,358,134.11 | 986,134.11 | F |
| Bank service charge | 542,147.22 | 4,766,271.16 | 4,224,123.94 | F |
| Bad debt expense | 829,803,106.19 | (1,652,390,338.19) | (2,482,193,444.38) | F |
| Annual leave payment | 2,200,000.00 | 7,738,958.13 | 5,538,958.13 | F |
| Licence fee | 49,500,000.00 | 48,719,978.04 | (780,021.96) | UNF |
| Severance payment | 3,190,000.00 | 6,804,343.44 | 3,614,343.44 | F |
| Tax on deposit | 8,165,427.36 | 12,650,837.10 | 4,485,409.74 | F |
| Member ship fee | 10,000.00 | 25,000.00 | 15,000.00 | F |
| Documentary Film | 2,000,000.00 | 37,257.00 | (1,962,743.00) | UNF |
| Tansportation | 0.00 | 1,313,329.92 | 1,313,329.92 | F |
| Consutant fee | 3,174,427.00 | 3,119,600.00 | (54,827.00) | UNF |
| Sponor ship | 3,400,000.00 | 635,722.00 | (2,764,278.00) | UNF |
| Funeral | 52,562.79 | 16,000.00 | (36,562.79) | UNF |
| Deprication | 41,597.887.46 | 25,765,529.27 | (15,832,358.19) | UNF |
| Discount loan int. | 0.00 | 17,487,378.23 | 17,487,378.23 | F |
| **Total General Expenses** | **970,986,023.73** | **(1,402,268,285.82)** | **(2,373,254,309.55)** | UNF |
| **Total Expenses** | **2,210,224,808.98** | **466,602,080.37** | **(1,743,622,728.61)** | UNF |
| **Net income (loss)** | **(357,754,843.74)** | **1,297,050,011.24** | **1,654,804,854.98** | F |

**NB: F= Favorable UN F = Un favorable**